# እንዴት ይብቃ?

ከአንተነህ መርዕድ

## በቃ! ገዬ! ያክል! አሎኒ! ዲታህ! ወጣንድም! በስ! ጊደስ!

በቃ የሚለው ቃል አገር ውስጥና ውጭ በምንገኝ ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ጎልቶ የሚነገር ክቡር ቃል ሆኗል። በዚህ ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ በያዘ ቃል ዙርያ በመንቀሳቀስ ተጨባጭ ሃይል ፈጥሮ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት የ "በቃ" ን መልዕት በሚገባ መረዳትን ይጠይቃል። በአገር ላይ ለውጥ ለማምጣት ይቅርና በግል ህይወት ዙርያም ለመንቀሳቀስ፣ የጠራ እምነትና ያንን እምነት ተግባራዊ ለማድረግ ጸንቶ መገኘት ያስፈልጋል። ያለዝያ አግባብ ያልሆነ መስዋእት ማብዛት ብሎም ውድቀትን መጋበዝ ነው። በኢትዮጵያ ለውጥ ለማምጣት እስካሁን የተከፈለው መስዋእት ቀላል አይደለም። ለምንመኘው ድል ያልበቃነው ግን በጠላቶቿ ጥንካሬ ሳይሆን ባመዛኙ በኛው ድክመት ነው። ስለዚህም በቃ ማለት ያለብን የራሳችንን ድክመት ይመስለኛል።

አምባገነኖች በሃገራችን ሆነ በዓለም ታሪክ ውስጥ "በግፍ መግዛቱ፣ ሰው መግደሉ፣ ሃብት አለአግባብ መዝረፉ በቃን" ብለው አያውቁም። ይህንን የምንጠብቅ ከሆነ ቢያንስ በየዋህነት ከነሱ የባሰ ወንጀል እየሰራን ነው። ደግሞም አብዛኛውን ጊዜ ስናደርግ የኖርነው ይህንኑ ነው። አምባገነኖች በቃችሁ ስለተባሉም አይሰሙም። ሩቅ ሳንሄድ በኛው የቅርብ ታሪክ እንመልከተው። ቀዳማዊ ኃይለስላሴ እድሜአቸው ሰማንያ ዓመት ሁሉ አልፏቸው በቃዎት በማለት ወዳጅ ዘመድ ሆነ ተቃዋሚ ቢለምናቸው ፍንክች አላሉም። ላገርም ለራሳቸውም ታሪክ በማይበጅ መልኩ ፍጻሜአቸውን አበላሹት። ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም አንድ ወጣት ትውልድ ከመፍጀት አልፈው ደጋፊዎቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ባንድ ጉድጓድ ከቀበሩ በኋላ ቀሪ ባለስልጣኖቻቸውንና የኢትዮጵያን ህዝብ አስረው ለወያኔና ለሻዕብያ በማስረከብ ተገደው ከስልጣን ተወግደዋል። መለስ የቀዳማዊ ኃይለስላሴንና የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ቤተመንግስት ብቻ ሳይሆን ባህሪና ድርጊታቸውን ጭምር ነው የወረሱት። በረሃ የጀመሩትን የብረት አገዛዝ ከመተግበር ወደኋላ አላሉም። የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ አይደለም፣ የገዛ ጓደኞቻቸውን ተራ በተራ ባካልም በፖለቲካውም ገድለዋቸዋል። በቃህ የሚለውን ቃል ልክ እንዳሁኖቹና እንደቀደምት አምባገነኖች የሚሰሙበት ጀሮ ሆነ የሚአስተውሉበት ህሊና የላቸውም። ፍጻሜአቸውም እንደሌሎቹ አምባገነኖች መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። ሳዳምን፣ ሙባረክን፣ ጋዳፊን ሆነ ሌሎችን የዓለም አምባገነኖችን አይተናል። ሁሉም አምባገነኖች ባንድ ልብ ባንድ አእምሮ የሚአስቡ እስኪመስሉ ተግባራቸው ተመሳሳይ ነው። ውድቀታቸውም እንዲሁ።

ጎበዝ! መልሱ ያለው በቃችሁ ከሚለው ወገን እንጂ ከነሱ እኮ አይደለም።

ለዚህ ደግሞ በቃችሁ ብቻውን በቂ አይሆንም። በቃችሁ ባይ መከበርና መፈራት የሚችልበት አቅም ሊኖረው ይገባል። ያ አቅም ደግሞ በራስ ድክመት ዙርያ በማተኮር ስህተትን አርሞ፣ ጥንካሬን አጎልብቶ፣ በቃችሁ ለማለት በቂ ሆኖ በመገኘት እንጂ በምኞትና ሲያደርሰን ቅዳሜና እሁድ በምናደርገው ጩኸት አይመጣም። ከትናንት ወንድምና እህቶቻችን ጋር በባህሪና በድርጊት አንድ ነን። ከትናንቶቹ ተሽለን ላለመገኘታችን አሁን ያለንበት ሁኔታ ምስክር ነው። "አንድ ህዝብ የሚገባውን መንግስት ያገኛል" የሚለው አባባል እውነትነት ያለው ይመስላል። "የግፍ አገዛዝ አይገባንም" የሚል ሁሉ ካምባገነኖች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መተባበር ሳይሆን ላገር በሚበጅ ጉዳይ ዙርያ መስማማትና መታገል አለበት። የራስን ድክመት በማረም ለለውጥ ራስን አዘጋጅቶ መገኘት ይገባል።

በሌሎች ላይ የሚፈጸመውን ግፍ አይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን ከማለፍ ዘለን የግፉ ተባባሪ እስከመሆን የደረስን ብዙ ነን። መንግስቱ ኃይለማርያም በየቤቱ እየሄዱ ሰው መግደል አላስፈለጋቸውም ነበር። እጃቸውንና አእምሮአቸውን ሆኖ የሚሰራላቸው በህዝቡ መካከል ሞልቶ ነበርና። መለስም ቢሆኑ እሳቸውን ሆኖና እሳቸውን አክሎ በውክልና ግፍ ለመፈጸም የተዘጋጀ በመካከላችን እስካለ ድረስ ጉልበታቸው አይደክምም። ግፉ በየግላችንና በየጓዳችን እስኪመጣ መጠበቅ፣ በሌሎች ላይ የሚፈጸመውን ኢሰባዊ ድርጊት እንዳላዩ ሆኖ ማለፍ ይዘገያል እንጂ ውጤቱ ራስን መጉዳት ነው። ጎረቤት ላይ እሳት ሲነሳ ለማጥፋት መተባበር ጎረቤትን ከማዳን የዘለቀ የራስ ጥቅም አለው። እኛ ግን በሌሎች ላይ የነደደው እሳት እንደማይደርስብን አንገታችንን ደፍተን እሳቱ በየቤታችን እስኪቀጣጠል እንጥብቃለን። ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ የተደረገው ጭፍጨፋ፣ ወላይታ አረካ ውስጥ ተደግሟል፤ ጋምቤላ የተፈጸመው ዘር ማጥፋት በወለጋ፣ በጅማና በአምቦ ግድያ ተመሳስሏል። በፓዊ፣ ወተር፣ አርባጉጉ፣ አጋዴን ሆነ አዲስ አበባ በንጹሃን ላይ ቃታ ለመሳብና ህይወት ለመቅጥፍ ስርአቱ አልሳሳም። ግን ሁላችንም በየቤታችንና በተከለለልን ቀበሌ ተወስነን አልቅሰናል። እሳቱ በየቤታችን እስኪነድ ጠብቀናል! ነዶም ሲአቃጥለን "የባሰ አታምጣብን" በማለት ጸሎት ላይ ነን።

የኢትዮጵያ ህዝብ የግፍ አገዛዝን ያልተቃወመበት ጊዜ የለም። ይሁን እንጂ ይህንን ፍላጎቱን ለማሳካት መሪና ድርጅት አላገኘም። ሩቅ ሳንሄድ ያለፉትን ሃያ አመታት ልምዳችንን እየተመለከትን ራሳችንን እንታዘብ። ኮሎኔል ጎሹ አምስት ሰው እንኳ አገር

ውስጥ ሳያዘጋጁ “ልዘምት ነው” ሲሉ ገንዘቡን፣ ወርቁን የለገሰው፣ እምባውን ያፈሰሰው፤ ልቡንም የሰጠው በውጭ አገር ሆነ በአገር ውስጥ ስንቱ ነበር? ኢዴሃቅ ብቅ ሲል በብዙዎቻችን ዘንድ ድጋፉና ተስፋው ምን ያህል ነበር? አማራጭ ኃይሎች አገር ውስጥ ሲቋቋምና ውጭ ሲንቀሳቀስ የነበረውን የሚረሳ ማን ነው? ሁሉም የህዝብ ድጋፍ ተችሯቸው የተጠበቀውን ያህል ውጤት ባለማምጣታቸው የህዝቡን ተስፋ አጨልመው አልፈዋል።

በሌላ በኩል ከታሪካዊው የግንቦት 1997ምርጫ ወቅት የተፈጠረው ቅንጅት ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያ ገኖ ሲወጣ ከወያኔ ጋር በመተባበር ከውጭና ከውስጥ በመረባረብ ድርጅቱ እንዲበታተን የብዙዎቹ አስተዋጽዖ እንደነበረበት የሚዘነጋ አይደለም። አሁንም ከድሮዎቹ ተቃዋሚዎች በተጨማሪ መድረክ፤ ግንቦት 7 እና የሌሎችንም ድርጅቶች እንቅስቃሴ እንዴት እያየንና እያገዝን ነው? እነዚህን ሁሉ ተቃዋሚዎች ለመፍጠርና ለመደገፍ፣ አስተዋጾ አድርገናል እንደምንል ቢገመትም፤ በሌላ በኩል ድርጅቶቹን ለመግደል፣ ለመበተን፣ የምንመኘውንም ድል ለማዘግየት የእኔም አስተዋጽዖ አለበት ብለን ለመቀበል ዝግጁ ካልሆንን አሁንም ትክክለኛ መስመር እየተከተልን  አይደለንም። እዚህ ላይ እውነተኛ መስዋእት የከፈሉትንና በመክፈል ላይ ያሉትን ጥቂቶችን ሳልዘነጋ ነው። ምን ያህልስ ለለውጥ ተዘጋጅተን  ነው ለውጥ ካልመጣ ብለን የምንጮኸው? አምባገነኖቻችንን ስለመቀየራቸው ከማውራታችን በፊት እስቲ ራሳችንን መጀመርያ እንቀይር። ለለውጥ ከባዱና መሰረታዊ እርምጃ ራስን ብቁ ማድረግ እንጂ ቀሪውማ ቀላል ነው። አምባገነኖች የኖሩት በኛ ድክመት እንጂ በነሱ ጥንካሬ አለመሆኑን እንረዳ። መለስ ከሙባረክ በላይ ጠንካራ አይደሉም። ጥያቄው እኛ እንደ ግብጾቹ፣ ቱኒሲያውያን፣ ሊብያውያን፣ የመኖች፣ ሶርያውያን ጠንካራና አንድ ነን ወይ? ነው!!

ወያኔዎች በየለቱ በሚፈጽሙት ገሃድ የወጣ ግፍ በቃችሁ መባላቸው የተገባ ነው። ፍጻሜአቸው ቅርብ ነው። መለስና ጓደኞቻቸው ብርክ ላይ ናቸው። ቀጭኗና ተንጠላጥለው የሚገኙባት የተስፋ ክራቸው የኛ አንድና ጠንካራ ሆኖ ያለመገኘት ድክመታችን ናት። የቱኒስያው ፕሬዝደንት የነበሩት ቤ አሊ የት ናቸው? አይደፈሬ ነኝ የሚሉት ሙባረክ በውርደትና በሞት አፋፍ ላይ ናቸው። ጋዳፊ ቀን ጨልሞባቸዋል። አንበሳ ነኝ ይሉ የነበሩት ያይቮሪኮስቱ ባግቦ በውርደት ከተደበቁበት በፍርሃት ሲርዱና ላብ ሲአጠምቃቸው በቴሌቪጅን እየተመለከቱ መለስም እያላባቸውና ቀን እየቆጠሩ እንደሆን ማን ይስተዋል? ግን ያንን ፍጻሜ ለማቅረብና ዘላቂና የማይነጠቅ ድል ሊኖረን የሚችለው በኛ አንድነትና ጥንካሬ ነው። በቃን የምንለው፤ የበቃን መሆኑን የምናረጋግጥበት ሃቅምና ጉልበታችን ለማደርጀት ምን እያደረግን ነው ብለን ራሳችንን እንጠይቅ!! እናም እንዘጋጅ።

ከግብጾቹና ከቱኒስያዎቹ ምን እንማራለን?

- **የትኩረት ማእከላቸው ጥቂት አምባገነኖች እንጂ በራሳቸው መካከል ያለው ልዩነት አይደለም**
  እኛም የጋራ ጠላት የሆነውን አምባገነን ስርዓት ለማስወገድ በጋራ መታገል እንጂ ጉልበትና ጊዜአችንን እርስ በርሳችን በምናደርገው ግብግብ ማባከን አይኖርብንም። ልዩነቶቻችን በመቀራረብና በመወያየት ከዚአም አልፎ በመተማመን የሚፈቱ ናቸው።
- **በዋናነት እርስ በርሳቸው መደጋገፍ መከባበር አሳይተዋል**
  በድርጅት ሆነ በግለሰብ ደረጃ መረዳዳት እንጂ መወነጃጀልና መሰዳደብ የትልቅነት ምልክት አይደለም። ደካሞችና ሰፊ ራእይ የሌላቸው ብቻ ናቸው ሌሎችን በማንኳሰስ ዙርያ የሚአተኩሩ። በራሱ የሚተማመን ግለሰብና ድርጅት ሌላን መጥላት አላማው አያደርግም። የጠራ አላማውን እያስረዳ ከመሰሎቹ ጋር በፍቅርና በመተባበር ራሱን ያደረጃል እንጂ።
- **ጠላት አላበዙም**
  ግብጾች አምባገነን ስራቱን አቅፎና ደግፎ ይዞ ያቆየውን ሁሉ ጠላታቸው አድርገው አልተነሱም። ባስተዋይነት መከላከያ ሰራዊቱን ከሙባረክ እጅ ፈልቅቀው ያወጡት በፍቅር ነው። እኛም በልበሰፊነት ከጥቂት አምባገነኖች በቀር ሌሎቹ የትግሉ አጋር እንዲሆኑ በሩን መክፈትና መገፋፋት እንጂ በግልብነት ሁሉንም በጠላትነት ማሰለፍ፣ ማዋረድ፣ ተስፋ ማሳጣት፣ ማንገላታት አይገባንም። አሁን የጋዳፊን የተቃዋሚ ጎራን ያጠናከሩት ብዙዎቹ ለጋዳፊ የሰሩ እንደነበሩ እያየን ነው። ለወያኔ ተገድዶ ሆነ አማራጭ አጥቶ የሚሰራ ሁሉ የህዝቡ አጋር እንዲሆን ከማበረታታት የተሻለ አማራጭ የለም።
- **ግብጾች ተስፋ ሳይቆርጡ እስከመጨረሻው ታግለዋል፤ አሁንም እየታገሉ ነው**
  አምባገኖች የመጨረሻዋን ኃይላቸውን አሟጥጠው በመጠቀም ተስፋ ሲአጡ ብቻ ነው የሚለቁት። ስለዚም ትግሉ መራራና ረጅም ሊሆን እንደሚችል መገንዘብና ለዚያ መዘጋጀት ተገቢ ነው። የሚወስዱትን ማንኛውንም እርምጃ በጽናት መቋቋም ብቻ ሳይሆን መቼ፣ ማን ላይ ምን እንደፈጸመ መረጃ በመሰብሰብ ማስተላለፍና ለዚያ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማብቃት አንዱና ዋናው ትግል ሊሆን ይገባል። ባንዱ ላይ የተፈጸመ ጥቃት በሌላውም ላይ የተቃጣ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም በሚችለው አቅምና ችሎታ ለትግሉ አስተዋጾ ማድረግ አለበት።
- **ግብጾች የምራዕቡን ድጋፍና ሚድያውን በትግስትና በጥበብ ተጠቅመውበታል**

ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት ባሁኑ ሰዓት አምባገነኖች የዜናውን ፍሰት ሊአቆሙ አልተቻላቸውም። የሙባረክ ጥረት እንዳልተሳካ አይተናል። ወያኔ የህዝብን አንደበት ለመዝጋትና በጨለማም ለመግዛት ያልፈነቀለው ደንጋይ የለም። በባህላዊውም ሆነ በዘመናዊ ዘዴ የትግሉን እንቅስቃሴ ማሰራጨትና የወያኔ ገበና ማጋለጥ አብዩ ተግባር መሆን አለበት። ሁሉም ዜጋ የራሱን አስተዋጾ ሳይንቅ በልዩ ልዩ ስልት መረጃ መቀበልና ማሰራጨት ይገባዋል።

በቃ ስንል ምኑ ነው የሚበቃው?ያምባገነን አገዛዝ? አዎ ይበቃል። የግፉ ጽዋ ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረ ዘመናት አስቆጥሯል። እኛ የግፉ ሰለባ የሆንነው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን ዓለም የተገነዘበው ነው። አሁን ላለንበት ሁኔታ ያበቃንን የኛን ድክመትም "በቃ"!! እንበለው። ከወያኔ የሚገኝ ፍርፋሪ ለመልቅም፣ ወይም በፍርሃት፣ ያለዚአም ተስፋ በመቁረጥ ለዚህ ስርዓት መቆየት አስተዋጾ በማድረግ ላይ ያለን ሁሉ ከሚሞት ስርዓት ጋር አብረን መሞት አይኖርብንም። ለህሊናም፣ ለታሪክም ከማይበጅ ድርጊት መቆጠብና በቃ ማለት ያለብን  አሁ ነው። ስንደግፍ ሆነ ስንነቅፍ ከስሜታዊነት ውጭ በማስተዋልና በመረጃ ተደግፈን ይሁን። የምደግፈው ወይም የምንነቅፈው ሃሳቡን እንጂ ግለሰቡ መሆን የለበትም። የተለመደው በግለሰብ ማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ባንድ ላለበቆማችንና ለውድቀታችን ምክንያት መሆኑን አንርሳው!!

በመጨረሻም በአጽንዖት ማስገንዘብ የምሻው ተቃዋሚ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል ብሄራዊ እርቅ ፈጥረው፤ ባንድ የጋራ መድረክ ዙርያ ተሰባስበው አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ጠንካራ የለውጥ ሃይል እንዲሆኑ ማብቃት ተገቢ ነው። ይህ እርምጃ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አንገብጋቢና ወቅቱ የሚሻው ጥያቄ ነው። ይህንን መንገድ እስካልተከተልን ድረስ በሀገራችን ያምባገነንነት ስር ዓት አብቅቶ ዴሞክራሲአዊ ባህል ይገነባል ብሎ ማሰብ አይቻልም።

ያምባገነንነትን አገዛዝ በቃ ስንል ለዚህ ያበቃንን የኛን ድክመትም በቃ እንበለው!!



እንዲያው ዝም፣ እንዲያው ዝም ይሻላል "መሌ"